# የአርበኞች ግንቦት 7 ስራ አስፈፃሚ ስራ መልቀቂያ!

(ከስር ያለው ፅሁፍ የአርበኞች ግንቦት 7 ስራ አስፈፃሚ አቶ አብርሃም ልጃለም የፃፈው ነው።)

“የአባቴ አብሮ አደግና ጓደኛ የነበሩት ዶክተር ላጲሶ ጌ ዴልቦ ስማቸውን በአማርኛ በማስቀየራቸው አሁን ለደረሱበት ከፍተኛ የትምህርት ማዕረግ ሲበቁ የኔ አባት ግን ስሜን ወደ አማርኛ አልለውጥም በማለቱ ምክንያት ሳይማር ቀረ” ብሎ ሰራዊት በተሰበሰበበት መሀል ለአንድ ህዝብ ያለውን የተለየ ጥላቻ የገለጸው የኤፍሬም ማዴቦ ዓይነት በአማራ ህዝብ ጥላቻ ከሰከረ ሰው ጋር አብሮ መስራት ቀርቶ አይኑን ማየት ስለማልሻ።”

የአርበኞች ግንቦት ሰባቱ የስራ አስፈጻሚ አባል ከድርጅቱ ሲለቅ 13 ምክንያቶችን አቅርቧል!

ድርጅቱን ጥሎ እንዲወጣ ምክንያት ናቸው ብሎ ከዘረዘራቸው 13 ነጥቦች መካከል የሚከተለውን ብሏል፡-

=======

እኔ አርበኛ ታጋይ አብርሀም ልጂአለም የህዝብ መብቶችና ጥቅሞች የሚከበሩበት የፖለቲካ ስርዓት በሀገራችን ለማስፈን የቀድሞው የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን በአፍላ የወጣትነት እድሜዬ በመቀላቀል ድርጅታዊ የፖለቲካ ትግልን ጀመርኩ።

በህዝብ ፍላጎትና ምርጫ የቆመ መንግስታዊ የፖለቲካ ስርዓት በሀገራችን ለማምጣት በተደረገው ፈታኝ ሰላማዊ ትግል ላይም እንደማናቸውም የትግል ጓዶቼ ዋጋ ከፍያለሁ። በዚህም ቅንጣት ታህል አልጸጸትም።

የድርጅቱን ኢዲሞክራሲያዊ አሰራር በመቃወም ከድረጅቱ የለቀቀው የአርበኞች ግንቦት 7 ስራ አስፈፃሚ አቶ አብርሃም ልጃለም

**ህወሀት በሰላማዊ ትግሉ የማይንበረከክ ሃይል እንደሆነ ባመንሁ ጊዜም ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ፋይዳው ታላቅ የሆነውን ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት በሀገራችን እውን ለማድረግ ከሚል መሰረታዊ እምነት በመነሳት ህወሃትን በትጥቅ ትግል ለመፋለም በ 2007 ዓ.ም ኤርትራ በረሃ በመውረድ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባርን ተቀላቀልኩ።**

በኢህአግ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በመሆን እስከ ውህደት የቆየሁ ሲሆን በኢህአግ እና ግንቦት 7 ውህደት ወቅት ደግሞ የንቅናቄው ምክርቤት እና የንቅናቄው ፍትህና ግልግል ኮሚቴ አባል በመሆን እስከ ነሀሴ 2009 ዓ/ም ድረስ አገልግያለሁ።

ከጳጉሜ 1 እስከ 5, 2009 ዓ.ም ድረስ በተደረገው አንደኛ መደበኛ የአግ 7 ንቅናቄው ጉባኤ ላይም ምክር ቤቱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል እንድሆን መርጦኝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የህዝባዊ እምቢተኝነቱ ዘርፍ ምክትል ሀላፊ በመሆን ወደ አገራችን እስከ ገባንበት ጊዜ ሳገለግል ቆይቻለሁ።

ባለፉት ፈታኝና አስቸጋሪ የትግል ዓመታትም ወያኔ በህዝባችን እና በሀገራችን ላይ እያደረሳቸው የነበሩ ጉዳቶችና በደሎች እንዲያበቁ ከታገልኩት ባልተናነሰ ስለ ህግ የበላይነትና በህግ ፊት ሊኖር ስለሚገባ እኩልነት እያወሩ የገዛ ድርጅታቸውን ህገ ደንብ የማያከብሩ የንቅናቄው ጉምቱ አምባገነኖችን በከፍተኛ የሞራል የበላይነት ከሌሎች የትግል ጓዶቼ ጋር በመሆን በሙሉ አቅሜ በግላጭ ታግያለሁ።

ይህን የመልቀቂያ ደብዳቤ እንዳዘጋጅና ከአግ 7 ንቅናቄ ራሴን በፈቃዴ እንዳሰናብት በርካታ ገፊ ምክንያቶቼን ከታች በዝርዝር የገለጽኩ ሲሆን የንቅናቄው አባላትና ደጋፊዎች ሊረዱት የሚገባ ትልቅ ቁም ነገር ቢኖር ንቅናቄውን በይፋ ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ድርጅቱ እንዲስተካከል የምችለውን ሁሉ ጥረት ማድረጌን ነው።

ነገር ግን ወደ አገር ቤት ከተገባ ጊዜ ጀምሮ መልቀቂያ ሳላቀርብ የቆየሁበት ዋና ምክንያት ከዛሬ ነገ ወደ ማስተዋልና ካለፈው ተምረው በስተታቸውም ተጸጽተው ሰራዊቱን በአግባቡ አነጋግረው ቦታ ያስይዙ ይሆናል በማለት ለዚህም ጊዜ መስጠቱ መልካም ነው ብዬ በማሰብ ነበር። ነገርግን ይህንን ከማድረግ ይልቅ ራስን ወደማግዘፍና ለቀጣዩ የፖለቲካ ዕቅዳቸው ገቢ በማሰባሰብ ስራ ላይ በመጠመዳቸው ምንም የሚለወጥ ስብዕና እንደሌላቸው ግልጽ ስላደረገልኝ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ደርሻለሁ።

በዚህም ምክንያት ከ 17/05/2011 አ/ም እስከ 18/05/2011 ዓ.ም ለተከታታይ 2 ቀናት በተካሄደው የንቅናቄው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ እንደማልገኝ በማሳወቅ በስብሰባው ላይ ሳልሳተፍ ቀርቻለሁ።

ንቅናቄውን እንድለቅ ካስገደዱኝ በርካታ ገፊ ምክንያቶች መካከል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

በአግ 7 ንቅናቄ እንዳልቀጥል ካደረጉኝ ገፊ ምክንያቶች መካከል:-

**1 ኛ)** የንቅናቄው ሊቀመንበር ብሄርን መሰረት በማድረግ በዙሪያቸው የሰበሰቧቸው ጥቂት የተመረጡ ግለሰቦችን ብቻ በማስጠጋት እንደ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ምክር ቤት፣የስራ አስፈጻሚውን እና የተለያዩ በጠቅላላ ጉባኤ የተቋቋሙ ኮሚቴወች በንቅናቄው መተዳደሪያ ደንብ በተሰጣቸው ስልጣን እና ተግባር መሰረት ሃላፊነታቸውን እንዳይወጡ እንቅፋት በመፍጠር፣ የንቅናቄው ስራ ላይ እንዳይሳተፉ በማግለል ፣ የንቅናቄውን የዕለት ተዕለት ስራ በህገደንቡ ስልጣን የተሰጠው አካል እንዳያስተባብር ፣እንዳይቆጣጠርና እንዳይመራ በር በመዝጋት፣ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ባላዘጋጀውና ምክር ቤቱ ባላጸደቀው በጀት ከድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ውጭ እየሰሩ መገኜታቸውና ንቅናቄውን እንደ ግል ንብረታቸው መጫወቻ ማድረጋቸው።

**2 ኛ)** የስራ አስፈጻሚና ጠቅላላ ጉባኤው በጋራ የወሰናቸውን ውሳኔወች በማን አለብኝነት ባለመከበራቸውና የንቅናቄውን መተዳደሪያ ደንብ በተደጋጋሚ መጣስ፣

**3 ኛ)** ሊቀመንበሩ በህግ ባልተሰጠው ውክልና እና ስልጣን በመጠቀም የሰራዊት አባላትን በማያውቀው የወታደራዊ ሙያ የሰራዊት አባላትን በወታደራዊ ዘመቻወች ላይ በማሰማራት ለአላስፈላጊ መሰዋዕትነት (እልቂት) እና እንግልት (በዕስርና በቶርቸር መጠበስ የአካል መጉደል የአንዳንድ ጓዶች የደረሱበት አለመታወቅ የሟች ቤተሰብ መበተን ሀብት ንብረት ሳይሰበሰብ ሜዳ መቅረት በጥይት የቆሰሉ ጓዶችን የሚያሳክማቸው አጥተው ለከፋ የአካልና የስነልቦና ጉዳት መዳረጋቸው ወዘተ (የዘመቻ መምሪያ ሀላፊ የነበሩት ኮማንደር አሰፋ ማሩ የእነ ገብርየን እና የአርባምንጩን ተልዕኮ አስመልክተው ያስገቡትን የመልቀቂያ ደብዳቤ ልብ ይሏል)

**4 ኛ)** ብረት አውርደው በሰላማዊ መንገድ በሀገር ውስጥ ለመታገል የገቡ እንደ ኦነግ አዲሃን ኦብነግ አይነት ድርጅቶች የሰራዊት አባላት መብቶችና ጥቅሞቻቸው እንዲከበር መሪወቻቸው ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቀጥታ በመነጋገርና በመደራደር የሰራዊታቸውን አለኝታነት በተግባር ሲያሳዩ የአግ **7** ሊቀመንበር ግን በደማቸው በቀይ ምንጣፍ ላይ ተረማምደውና ተከብረው በህዝብ ፊት በኩራት እንዲቆሙ ያስቻሏቸውን የሰራዊት አባላት የት ወደቃችሁ ብሎ ለማየት እንኳ መጸየፋቸው፣

**5 ኛ)** "የአባቴ አብሮ አደግና ጓደኛ የነበሩት ዶክተር ላጺሶ ጌ ዴልቦ ስማቸውን በአማርኛ በማስቀየራቸው አሁን ለደረሱበት ከፍተኛ የትምህርት ማዕረግ ሲበቁ የኔ አባት ግን ስሜን ወደ አማርኛ አልለውጥም በማለቱ ምክንያት ሳይማር ቀረ" ብሎ ሰራዊት በተሰበሰበበት መሀል ለአንድ ህዝብ ያለውን የተለየ ጥላቻ የገለጸው የኤፍሬም ማዴቦ ዓይነት በአማራ ህዝብ ጥላቻ ከሰከረ ሰው ጋር አብሮ መስራት ቀርቶ አይኑን ማየት ስለማልሻ።

**6 ኛ)** የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲመረጥ አጠቃላይ የድርጅቱን አለማቀፋዊ የፋይናንስም ሆነ የሰው ሃይል ለመምራትና ለማስተዳደር ጭምር ሆኖ ሳለ ሊቀመንበሩ የውጩን ፋይናንስ ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እውቅና እና ክትትል ውጭ በመሰወር ባለሚሎቻቸውን አጠቃላይ በተለያየ መንገድ ከአባላት ከሚሰበሰብ ገቢ **29%**ቱ እንዲከፈላቸው በጥቅም በማሰር የራሱ ጥቅመኛ ሰወችን በማስቀመጥ ገቢና ወጭው የማይታወቅ ግልጽ ያልሆነና ሊቀመንበሩ እንደ ግሉ ካዝና እንደፈለገ የሚጫወትበት የፋይናንስ አሰራር እስካሁን ድረስ ባለመስተካከሉና በትግሉ ስም ካገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተሰበሰበ ገንዘብ የፖለቲካ ነጋዴወች መበልጸጊያ በመሆኑ፣

**7 ኛ)** በአንድነት ስም የአማራን ህዝብ ትግል በዜሮ የሚያበዙ እውቅናን የሚነፍጉ በሊቀመንበሩ ጽ/ቤት ስር የተደራጁት የስትራቴጂክና ፕላን ክፍል አባላት ያላቸው የተሳሳተ ምልከታ።

**8 ኛ)**ቴክኒካል ኮሚቴው በሊቀመንበሩ በኩል የአማራን ህዝብ በብሄር መደራጀት አስመልክቶ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀረበው ትንታኔ የአማራውን በብሄር መደራጀት አጥብቆ የሚኮንንና የአማራ ህዝብ በብሄር መደራጀት በኢትዮጵያ ያለን ማንኛውም የፖለቲካ ሀይል ሁሉ ጠርጎ ዳግም የአማራውን ገዥ መደብ አገዛዝ ያሰፍናል ተብሎ እንደ ድርጅት በአቋም ደረጃ መያዙ። ይህ አመለካከት እንዲስተካከል ተደጋጋሚ ክርክሮችና ውይይቶች ቢካሄዱም እንኳን የቴክኒካል ኮሚቴው እይታ እንደሆነ አድርጎ አድበስብሶ ማለፍ።

**9 ኛ)** በወልድያ ቆቦና መርሳ ላይ በወያኔ ህወሃት አማካኝነት በንጹሀን ዜጎች ላይ የደረሰውን ግድያና ጭፍጨፋ በማውገዝ ለህልውናቸው ከተዋደቁ ወገኖቻችን ጎን ከመቆም ይልቅ ህወሃት የሰላም ጥሪ ያቀርብልኛል ከሚል ከንቱ ምኞት በመነሳት የትግራይ ህዝብ ዘርን መሰረት ያደረገ ጥቃት በአካባቢው ላይ እንደደረሰበት የሚገልጽ መግለጫ የአማራ ብሄር ተወላጅ የሆኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን በማግለል አቶ ቸኮል ጌታሁን አቶ አበበ ቦጋለ አቶ ኤፍሬም ማዴቦና ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ከትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ጋር በጋራ በመሆን ያወጡት አሳፋሪ መግለጫ በወቅቱ ብዙ ያወዛገበን ቢሆንም ከአሁኑ ባህሪያቸው ጋር ሲገናኝ ንቅናቄውን እንደ ግል ንብረት የሚያዙበት ግልጽ ሁኔታ መኖሩና እነዚህ አንጋፋ አመራሮች በአማራ ብሄር ላይ ያላቸውን አግላይ አቋም ማሳያ እንደሆነ በግልጽ ስለተረዳሁ፣

**9 ኛ)** አገራችን ከገባን በኋላም የድርጂቱን ከፍተኛ አመራሮች ከስራና ከድርጂታዊ ሃላፊነታቸው በመነጠል ደህንነታቸውን ስጋት ላይ መጣል

**10 ኛ)**ከህገ ደንብ ውጭና ም/ቤቱ አመራሩ መመሪያና ውክልና ሳይሰጥ በማናለብኝነት ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ውህደት ለማድረግ መጣደፍ እንዲሁም የራስን መሰረታዊ ችግር በሌሎች ፓርቲዎች ለመሸፈን መፍጨርጨር

**11** ኛ) አመራሩን ከድርጂታዊ መረጃ ደሃ አድርገው ድርጂታዊ ጉዳዩዎችን ከሚዲያ እንዲሰማና የባይተዋርነት ስሜት እንዲፈጠርበት ማድረግ እንዲያም ሲል የግል ዝናን ከፍ ለማድረግ በራሳቸው ገጽ መልቀቅ

**12** ኛ) ከነ ዶ/ር አብይ ጋር የሚደረገውን ድርድር በተመለከተ ስ/አስፈጻሚው ተወያይቶ ተደራዳሪዎችን ይሰይማል የሚል ስምምነት የነበረ ቢሆንም አፈጻጸሙ ከዚህ የተለየ መሆኑ

**13** ኛ) ሊቀመንበሩና የሱ ጋሻ ጃግሬዎች ብቻ ስ/አስፈጻሚ ኮሚቴው ሳያውቅ ከድርጂት መርህ ውጭ ወደ አውሮፓና አሜሪካ ጉዞ ማድረግ። የሚጠቀሙት በጀትም በፋይናንስ አሰራር መርህን ያልተከተለና ኦዲት መደረግ የሚችልበትን አሰራርም አለመኖር ምክንያቶቹ በትንሹ እነዚህ ሲሆኑ በማወቅም ይሁን ባለማቅ በዚህ የትግል ሂደት ላይ የበደልኳቹሁ ያስቀየምኳችሁ ያስከፋኋቹሁ ሁሉ ከልብ የመነጨ ይቅርታን እጠይቃቹሃለሁ።

(አንደማርያም ዕዝራ ገፅ ላይ)